# በአማርኛ እንዴት ታይፕ አደርጋለሁ?

የአማርኛ ፊደላትን በኮምፒውተር ታይፕ ለማድረግ ተቀራራቢነት ያላቸውን የእንግሊዝኛ ፊደላትን በመጠቀም መምታት ይቻላል። ይህም «phonetic» ይባላል። ፊደሉ በአማርኛ ምን አይነት ድምጽ እንዳለው በማሰብ የእንግሊዘኛ ቁልፎቹን በኮምፒውተሩ ሰሌዳ ላይ በመጠቀም የመምታት ዘዴ ነው።

ለምሳሌ፡- «selam» የሚለውን ቃል ታይፕ ለማድረግ «ሰላም» ይሆናል።

አማርኛ ከእንግሊዝኛ የበለጠ ብዙ ድምጽ ወይም ፊደል ስላለው አንዳንድ ጊዜ የሚወክለውን ፊደል መለየት ያዳግታል። በመሆኑም ተጨማሪ ህግ ያስፈልገዋል። ለምሳሌ ‹ጠ›ን ታይፕ ለማድረግ በእንግሊዘኛ ለብቻው የተወከለ ፊደል ስለሌለው በተቀራታቢነት ‹t›ን እንጠቀማለን። ነገር ግን ‹t› በጣም የሚቀርበው ለ‹ተ› ፊደል በመሆኑ ትልቁን (capital) ‹T›ን በመጠቀም የምንፈልገውን ፊደል ማለትም ‹ጠ›ን እናገኛለን።

ለምሳሌ፡- «TienaysTlN» – «ጤናይስጥልኝ» ይሆናል።

ከላይ በተመለከተው ምሳሌ ላይ ትልቁን (capital) ‹N›ን በመጠቀም ‹ኝ› ፊደልን ማግኘታችን ያስተውሉ። እንዲሁም ‹ie› በአንድነት በመጠቀም የ‹ጠ› አምስተኛ ፊደል ‹ጤ› አስገኝቶናል። በዚህ ሁኔታ የሚፈልጉትን ቃል ለማግኘት በድምጽ ቅርበት ያለውን የእንግሊዘኛ ፊደል በመጫን፣ አልያም (capital) ትልቁን ፊደል ይህም ካለሆነ ደግሞ የፊደሉን ቁልፍ ሁለት ጊዜ ደግሞ በመጫን ይሆናል።

ለምሳሌ፡- «sselam» – «ሠላም» ይሆናል።
«SSeHey» – «ፀሐይ» ይሆናል።

በመጨረሻ ልናስረዳ የምንፈልገው የ‹አጣቃሽ› ወይም “ ’ ” (apostrophe)ን ለየት ያለ ህግ ነው። የአንዳንድ ቃላቶች አወቃቀር ሳድስ ሆኖ በአናባቢ ወይንም (vowel) ሲቀጠል የአጣቃሽ ምልክቱን መጠቀም ግድ ይሆናል። አለበለዚያ ግን ከፊት ለፊት የመታነውን ‹ሳድስ› ፊደል ይቀይረዋል። ይህንን ለማሳየት እንዲረዳ «ገብ<u>ርኤ</u>ል» የሚለውን ቃል ለመምታት ከ‹ር› ፊደል በኋላ አጣቃሹን ከዚያ ደግሞ ‹ኤ›ን በመጠቀም «geb<u>r'E</u>l» በማለት እናስቀምጣለን። አጣቃሹን ባንጠቀም ግን ‹ር› ወደ ‹ሬ› ይቀየራል።

ለምሳሌ፡- «mel'ak» – «መልአክ» ይሆናል።
«m'eeraf» – «ምዕራፍ» ይሆናል።

ይህንን አጣቃሽ ምልክት ለአማርኛ (Ethiopic) ቁጥሮችም ጠቀሜታ አለው። በዚሁም መሰረት '1-፩ ይሆንና ሌሎቹም በዚሁ መልክ ያገኛሉ። እራሱ አጣቃሹን “ ’ ” ለመጠቀም ደግሞ ምልክቱን ሁለት ጊዜ ደግሞ በመምታት ይሆናል። ይህ ዘዴ ለሌሎችም ምልክቶች (punctuation) ይጠቅማል። በዚሁ ሁኔታ ይህንን ምልክት ‹;› በመሆን በመጀመሪያ ጊዜ ሲመታ ‹፤› የአማርኛ ፊደሉን (ምልክቱን) ሲያስገኝ፣ ደግመው ሲመቱት ደግሞ የእንግሊዘኛውን ምልክት ‹;› ያስገኛል።

ከዚህ በታች የሚታየው ሰንጠረዥ ጠቅላላውን የአማርኛ ፊደላት፣ ቁጥሮችና ምልክቶች እንዴት ታይፕ ማድረግ እንደሚቻል ያሳያል።

# Amharic Typing Table

| ቤተሰብ | ግዕዝ | ካዕብ | ሣልስ | ራብዕ | ኃምስ | ሳድስ | ሳብዕ | ዘመደ-ግዕዝ | ዘመደ-ካዕብ | ዘመደ-ሣልስ | ዘመደ-ራብዕ | ዘመደ-ኃምስ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ሆይ | ሀ he | ሁ hu | ሂ hi | ሃ ha | ሄ hie | ህ h | ሆ ho | | | | | |
| ላዊ | ለ le | ሉ lu | ሊ li | ላ la | ሌ lie | ል l | ሎ lo | | | | ሏ lua | |
| ሐውት | ሐ He | ሑ Hu | ሒ Hi | ሓ Ha | ሔ Hie | ሕ H | ሖ Ho | | | | ሗ Hua | |
| ማይ | መ me | ሙ mu | ሚ mi | ማ ma | ሜ mie | ም m | ሞ mo | | | | ሟ mua | |
| ሠውት | ሠ sse | ሡ ssu | ሢ ssi | ሣ ssa | ሤ ssie | ሥ ss | ሦ sso | | | | ሧ ssua | |
| ርእስ | ረ re | ሩ ru | ሪ ri | ራ ra | ሬ rie | ር r | ሮ ro | | | | ሯ rua | |
| ሳት | ሰ se | ሱ su | ሲ si | ሳ sa | ሴ sie | ስ s | ሶ so | | | | ሷ sua | |
| ሻ-ሳት | ሸ xe | ሹ xu | ሺ xi | ሻ xa | ሼ xie | ሽ x | ሾ xo | | | | ሿ xua | |
| ቃፍ | ቀ qe | ቁ qu | ቂ qi | ቃ qa | ቄ qie | ቅ q | ቆ qo | ቈ que | ቊ qui | ቍ quu | ቋ qua | ቌ quie |
| ቤት | በ be | ቡ bu | ቢ bi | ባ ba | ቤ bie | ብ b | ቦ bo | | | | ቧ bua | |
| ቬ-ቤት | ቨ ve | ቩ vu | ቪ vi | ቫ va | ቬ vie | ቭ v | ቮ vo | | | | ቯ vua | |
| ታው | ተ te | ቱ tu | ቲ ti | ታ ta | ቴ tie | ት t | ቶ to | | | | ቷ tua | |
| ቻ-ታው | ቸ ce | ቹ cu | ቺ ci | ቻ ca | ቼ cie | ች c | ቾ co | | | | ቿ cua | |
| ኀርም | ኀ hhe | ኁ hhu | ኂ hhi | ኃ hha | ኄ hhie | ኅ hh | ኆ hho | ኈ hue | ኊ hui | ኍ huu | ኋ hua | ኌ huie |
| ነሐስ | ነ ne | ኑ nu | ኒ ni | ና na | ኔ nie | ን n | ኖ no | | | | ኗ nua | |
| ኛ-ነሐስ | ኘ Ne | ኙ Nu | ኚ Ni | ኛ Na | ኜ Nie | ኝ N | ኞ No | | | | ኟ Nua | |
| አልፍ | አ a | ኡ u | ኢ i | ኣ ea | ኤ ie | እ e | ኦ o | ኧ ea | | | | |
| ካፍ | ከ ke | ኩ ku | ኪ ki | ካ ka | ኬ kie | ክ k | ኮ ko | ኰ kue | ኲ kui | ኵ kuu | ኳ kua | ኴ kuie |

| | | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ኻ-ካፍ | ኸ<br>Ke | ኹ<br>Ku | ኺ<br>Ki | ኻ<br>Ka | ኼ<br>Kie | ኽ<br>K | ኾ<br>Ko | | | | | |
| ወዌ | ወ<br>we | ዉ<br>wu | ዊ<br>wi | ዋ<br>wa | ዌ<br>wie | ው<br>w | ዎ<br>wo | | | | | |
| ዐይን | ዐ<br>aaa | ዑ<br>uu | ዒ<br>ii | ዓ<br>aa | ዔ<br>iie | ዕ<br>ee | ዖ<br>oo | | | | | |
| ዘይ | ዘ<br>ze | ዙ<br>zu | ዚ<br>zi | ዛ<br>za | ዜ<br>zie | ዝ<br>z | ዞ<br>zo | | | | ዟ<br>zua | |
| ዠ-ዘይ | ዠ<br>Ze | ዡ<br>Zu | ዢ<br>Zi | ዣ<br>Za | ዤ<br>Zie | ዥ<br>Z | ዦ<br>Zo | | | | ዧ<br>Zua | |
| የመን | የ<br>ye | ዩ<br>yu | ዪ<br>yi | ያ<br>ya | ዬ<br>yie | ይ<br>y | ዮ<br>yo | | | | | |
| ድንት | ደ<br>de | ዱ<br>du | ዲ<br>di | ዳ<br>da | ዴ<br>die | ድ<br>d | ዶ<br>do | | | | ዷ<br>dua | |
| ጅ-ድንት | ጀ<br>je | ጁ<br>ju | ጂ<br>ji | ጃ<br>ja | ጄ<br>jie | ጅ<br>j | ጆ<br>jo | | | | ጇ<br>jua | |
| ገምል | ገ<br>ge | ጉ<br>gu | ጊ<br>gi | ጋ<br>ga | ጌ<br>gie | ግ<br>g | ጎ<br>go | ጐ<br>gue | ጒ<br>gui | ጕ<br>guu | ጓ<br>gua | ጔ<br>guie |
| ጠይት | ጠ<br>Te | ጡ<br>Tu | ጢ<br>Ti | ጣ<br>Ta | ጤ<br>Tie | ጥ<br>T | ጦ<br>To | | | | ጧ<br>Tua | |
| ጨ-ጠይት | ጨ<br>Ce | ጩ<br>Cu | ጪ<br>Ci | ጫ<br>Ca | ጬ<br>Cie | ጭ<br>C | ጮ<br>Co | | | | ጯ<br>Cua | |
| ጰይት | ጰ<br>Pe | ጱ<br>Pu | ጲ<br>Pi | ጳ<br>Pa | ጴ<br>Pie | ጵ<br>P | ጶ<br>Po | | | | ጷ<br>Pua | |
| ጸደይ | ጸ<br>Se | ጹ<br>Su | ጺ<br>Si | ጻ<br>Sa | ጼ<br>Sie | ጽ<br>S | ጾ<br>So | | | | ጿ<br>Sua | |
| ፀጻ | ፀ<br>SSe | ፁ<br>SSu | ፂ<br>SSi | ፃ<br>SSa | ፄ<br>SSie | ፅ<br>SS | ፆ<br>SSo | | | | | |
| አፍ | ፈ<br>fe | ፉ<br>fu | ፊ<br>fi | ፋ<br>fa | ፌ<br>fie | ፍ<br>f | ፎ<br>fo | | | | ፏ<br>fua | |
| ፐሳ | ፐ<br>pe | ፑ<br>pu | ፒ<br>pi | ፓ<br>pa | ፔ<br>pie | ፕ<br>p | ፖ<br>po | | | | ፗ<br>pua | |
| | | | | | | | | | | | | |
| | ፡<br>: | ።<br>:: | ፣<br>, | ፤<br>; | ፥<br>,, | ፦<br>:- | | | | '<br>' ' | ,<br>,,, | ;<br>;; |
| | ፩<br>'1 | ፪<br>'2 | ፫<br>'3 | ፬<br>'4 | ፭<br>'5 | ፮<br>'6 | ፯<br>'7 | ፰<br>'8 | ፱<br>'9 | | | |
| | ፲<br>'10 | ፳<br>'20 | ፴<br>'30 | ፵<br>'40 | ፶<br>'50 | ፷<br>'60 | ፸<br>'70 | ፹<br>'80 | ፺<br>'90 | ፻<br>'100 | ፲፻<br>'1000 | ፼<br>'10000 |

# የተለያየ ቋንቋን ታይፕ የማድረግ ዘዴ

ዩኒኮድ የተሰኘው ዘዴ ከተፈጠረ በኋላ በርካታ የአማርኛ ፊደላትን በኮምፒውተር ለመምታት አስችሏል። ይኸው ዩኒኮድ በተለያዩ ቋንቋዎች 461 የኢትዮጲክ ፊደላትን ለመጻፍ ያስችላል። ይህም በጣም ብዙ ፊደላት ስለሆኑ በአማርኛ የታይፕ ሰሌዳ ላይ ያልተፈለገ ቃላትን ላለመፍጠር ሲባል ይህ የዩኒኮድ ዘዴ አይሰራም። ነገር ግን እነኝህን የኢትዮጲክ ፊደላት መጠቀም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ይህንን የዩኒኮድ የታይፕ ሰሌዳን መጠቀም ይቻላል።

ዩኒኮድን ለመጠቀም ሁለት አይነት መንገድ አለው።

1. Ctrl + Alt + Yን በአንድነት በመምታት፣ ይህን ምልክት የታችኛው ታስክ ባር ላይ እንዲመጣና ዩኒኮድን ለመተቀም ዝግጁ መሆኑን ያሳያል።
2. በታስክ ባሩ ላይ ይህንን ምልክት በመጫን ከዚያም ደግሞ ይህንን ምልክት በተከታታይነት በመጫን የታይፕ ሰሌዳውን ለዩኒኮድ ማዘጋጀት ይቻላል።

ሌሎች ቋንቋዎችን እንዴት ታይፕ እንደሚደረግ ከዚህ በታች ይታያል።

## Awngi/Blin/Kayla/Kufal/Quara/Qimant/Xamtanga

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ጘ Ge | ጙ Gu | ጚ Gi | ጛ Ga | ጜ Gie | ጝ G | ጞ Go |
| ⶓ Gue | ⶖ Guu | ⶔ Gui | ጟ Gua | ⶕ Guie | | |

## Bench

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ⶠ xxe | ⶡ xxu | ⶢ xxi | ⶣ xxa | ⶤ xxie | ⶥ xx | ⶦ xxo |
| ⶨ cce | ⶩ ccu | ⶪ cci | ⶫ cca | ⶬ ccie | ⶭ cc | ⶮ cco |
| ⶰ ZZe | ⶱ ZZu | ⶲ ZZi | ⶳ ZZa | ⶴ ZZie | ⶵ ZZ | ⶶ ZZo |
| ⶸ CCe | ⶹ CCu | ⶺ CCi | ⶻ CCa | ⶼ CCie | ⶽ CC | ⶾ CCo |

## Ge’ez

| ይዘት | ደረት | ርክርክ | ኅጺር፡ ርክርክ | ድፋት | ቅናት | ጭረት | ሒደት | ቁርጥ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ᎐<br>_1 | ᎑<br>_2 | ᎒<br>_3 | ᎓<br>_4 | ᎔<br>_5 | ᎕<br>_6 | ᎖<br>_7 | ᎗<br>_8 | ᎙<br>_0 |

| | | |
|---|---|---|
| ፧<br>? | ፠<br>:+ | ፨<br>:# |

የግዕዝ ቁጥሮችም በዚሁ በዩኒኮድ ዘዴ በመጠቀም ታይፕ ማድረግ ይቻላል። ይህንንም በምናደርግ ጊዜ ከፊት ለፊቱ አጣቃሹን “ ’ ” ታይፕ ማድረግ አያስፈልገንም። ይህኛው መንገድ በጥቂቱም ቢሆን ቀላል ዘዴ ነው።

## Me’en/Mursi/Suri

| | | | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ሇ<br>hoa | ⶀ<br>loa | ⶁ<br>moa | ⶂ<br>roa | ⶃ<br>soa | ⶄ<br>xoa | ቇ<br>qoa | ⶅ<br>boa | ⶆ<br>toa | ⶇ<br>coa | ኇ<br>hhoa | ⶈ<br>noa | ⶉ<br>Noa | ⶊ<br>oa |
| ኯ<br>koa | ዏ<br>woa | ⶋ<br>zoa | ዯ<br>yoa | ⶌ<br>doa | ⶍ<br>Doa | ⶎ<br>joa | ጏ<br>goa | ⶏ<br>Toa | ⶐ<br>Coa | ⶑ<br>Poa | ጟ<br>SSoa | ⶒ<br>poa | |

## Me’en/Mursi/Suri/Dizi & Historical Oromo/Sidama

| | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ዸ<br>De | ዹ<br>Du | ዺ<br>Di | ዻ<br>Da | ዼ<br>Die | ዽ<br>D | ዾ<br>Do | ዿ<br>Dua |

## Sebatbeit

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ⷀ<br>qye | ⷁ<br>qyu | ⷂ<br>qye | ⷃ<br>qye | ⷄ<br>qye | ⷅ<br>qye | ⷆ<br>qyo |
| ⷈ<br>kye | ⷉ<br>kyu | ⷊ<br>kyi | ⷋ<br>kya | ⷌ<br>kyie | ⷍ<br>ky | ⷎ<br>kyo |
| ⷐ<br>Kye | ⷑ<br>Kyu | ⷒ<br>Kyi | ⷓ<br>Kye | ⷔ<br>Kyie | ⷕ<br>Ky | ⷖ<br>Kyo |
| ⷘ<br>gye | ⷙ<br>gyu | ⷚ<br>gyi | ⷛ<br>gya | ⷜ<br>gyie | ⷝ<br>gy | ⷞ<br>gyo |

| |
|---|
| ᎃ<br>mue |
| ᎇ<br>bue |
| ᎋ<br>fue |
| ᎏ<br>pue |

| |
|---|
| ᎁ<br>mui |
| ᎅ<br>mue |
| ᎉ<br>fue |
| ᎍ<br>pue |

| | |
|---|---|
| ᎂ<br>muie | ᎀ<br>muu |
| ᎆ<br>buie | ᎄ<br>buu |
| ᎊ<br>fuie | ᎈ<br>fuu |
| ᎎ<br>puie | ᎌ<br>puu |

## Tigrinya

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ቐ<br>Qe | ቑ<br>Qu | ቒ<br>Qi | ቓ<br>Qa | ቔ<br>Qie | ቕ<br>Q | ቖ<br>Qo |
| ቘ<br>Que | ቝ<br>Quu | ቚ<br>Qui | ቛ<br>Qua | ቜ<br>Quie | | |
| ዀ<br>Kue | ዅ<br>Kuu | ዂ<br>Kui | ዃ<br>Kua | ዄ<br>Kuie | | |

# የአማርኛ ሶፍትዌሩን ለመጫንና ለመጠቀም

**ይህ ፋይል AmharicPowerPack7.exe ሶፍትዌሩን Tavultesoft Keymanንና ፎንቱን (የኮምፒውተር ፊደላቱን) የያዘ ነው። የሶፍትዌሩ አጫጫን ዘዴም እንደሚከተለው ይሆናል፡-**

1. **ሁለት ጊዜ ደግመው ይጫኑትና የአጫጫኑን ትዕዛዝ በሚገባ ይከተሉ**
2. **ሶፍትዌሩን በሚገባ ከጫኑ በኋላ "ፕሮግራም" ስር Tavultesoft Keymanንን ያገኛሉ። ፕሮግራሙን ለመጀመር፡-**

   **በመጀመሪያ Start > ከዚያ All Programs**

   **> ከዚያ Tavultesoft Keyman Desktop Light 7.1**

   **> ከዚያ Keyman Desktop Light 7.1 ይጫኑ**

3. **በታስክ ባሩ በቀኝ በኩል የሚታየውን ይህን ምልክት  መጫን**
4. **ይህን ሲያደርጉ የሚመጣው መስኮት ላይ የሚታየውን ይህንን ምልክት  መምረጥ**
5. **የኢትዮጲክ ፊደልን (ፎንት) መምረጥና ታይም ማድረግ ይቻላል**